# ፕሮፌሰር በለጠ ሞላ የአብን ሊቀመንበር

ረዳት ፕሮፌሰር በለጠ ሞላ የአብን ሊቀመንበር እንዲሁም አቶ ክርስቲያን ታደለ ደግሞ የፖለቲካ ጉዳዮች ኃላፊ ሆነው ተሾሙ።

አማራ ሚድያ ማዕከል/አሚማ
የካቲት 16 ቀን 2012 ዓ.ም አዲስ አበባ ሸዋ

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) የካቲት 14 እና 15 ቀን 2012 ዓ.ም ያካሄደው 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የንቅናቄውን የሥራ አስፈፃሚ አባላት በመምረጥ ተጠናቀቀ።

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ የካቲት 14 እና 15 ቀን 2012 ዓ.ም 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔውን የምርጫ ቦርድ ታዛቢ በተገኘበት በደብረ ብርሃን ከተማ አካሂዷል።

ጉባዔውን በንግግር የከፈቱት የንቅናቄው ሊቀመንበር ዶ/ር ደሳለኝ ጫኔ አብን የአማራን ሕዝብ ጥያቄ መመለሥ በሚያስችለውና ወቅቱ በሚፈልገው ልክ ይገኝ ዘንድ ላለፉት ጊዜያት የመጣበትን መንገድ መርምሮ በጥናት ላይ የተመሰረተ መዋቅራዊ ማሻሽያ መዘጋጀቱን ገለፀው በዚህ ላይ ጠቅላላ ጉባዔው በደንብ ተወያይቶ አቋም እንዲይዝበት ጠይቀዋል።

ጉባዔው በመጀመሪያ ቀን ውሎው የአብን መዋቅራዊ ማሻሽያ(ሪፎርም) አስፈላጊነትና አላማ፣ የንቅናቄው ጥቅል የሥራ ክንውን ሪፖርት፣ የፋይናንስ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ሪፖርት፣ የብሔራዊ ም/ቤቱ ሪፖርት፣ የተሻሻለው የንቅናቄው መተዳደሪያና ደንብ ቀርቦ በጠቅላላ ጉባዔው አባላት ሰፊ ውይይት ካደረገ በኃላ አፅድቋል።

ጠቅላላ ጉባዔው 5 ተለዋጭ አባላት ያሉት 45 የንቅናቄውን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥም መርጦ ያፀደቀ ሲሆን የተመረጡት አባላትም የድርጅቱን ሊቀመንበርና ም/ሊቀመንበር መርጠዋል። በተጨማሪም በሊቀመንበሩ የቀረቡለትን ብሔራዊ ሥራ አስፈፃሚዎችን አፅድቋል።
በዚህም መሰረት 9ኙ የአብን ሥራ አስፈፃሚ አመራሮች፡-

1. ረዳት ፕሮፌሰር በለጠ ሞላ ሊቀመንበር
2. አቶ የሱፍ ኢብራሂም ም/ሊቀመንበር
3. አቶ አዲስ ኃረገወይን የፖሊሲ ስትራቴጂ ኃላፊ
4. አቶ ጣሂር ሞሐመድ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ
5. ዶ/ር ቴዎድሮስ ኃ/ማርያም የውጭ ጉዳይና ዓለማቀፍ ግንኙነት

6. አቶ ጋሻው መርሻ የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ
7. አቶ መልካሙ ፀጋዬ የፅሕፈት ቤት ኃላፊ
8. አቶ ጥበበ ሰይፈ የሕግና ሥነምግባር ኃላፊ
9. አቶ ክርስቲያን ታደለ የፖለቲካ ጉዳዮች ኃላፊ ሆነው ተሾመዋል።